የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

# ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ መግለጫ

ታህሳስ 18/2010

## ሕዝብን በመግደልና በማፈን ሰላም አይመጣም

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር በአማራ ክልል፣በኦሮሚያና በኢትዮ ሶማሌ ክልል በአንባገነኑ የወያኔ መንግስት አገልጋይ አጋዚ ጦር እየተፈጸመ ያለውን ግድያና አፈና እንዲሁም እስራት የተጀመረውን ትግል ያጠብቀዋል እንጂ ቅንጣት ታህል አያበርደውም።

በሃገራችን ኢትዮጵያ እየተቀጣጠለ ያለው የመናገር ፣የመጻፍ ፣ የመሰብሰብ ነጻነት እና ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ህዝባችን ተገፎ መሪዎቹና ጦማሪዎቹ በሃሰት ውንጀላ ተከሰው ለበርካታ ዓመታትና ወራት በእስር እየተሰቃዩ ለመሆኑ የአደባባይ ሚስጢር ነው።

ህዝባችን ጦም ውሎና ጦም አድሮ ያሳደገውን ልጁን ተናገረ ተብሎ የሚገደልበት፣እናት ልጇ እሬሳ ላይ እንድትቀመጥ ተገዳ የምታለቅስበት፣ቁስለኞች በቤተሰባቸው ፊት በጥይት ተደብድበው የሚገደሉበት ፣ህግ አልባው መንግስት ዜጎችን በመሳሪያ አስገድዶ አስሮና አዋርዶ ወደ ማሰቃያ እስር ቤት የሚልክበት ሃገር ቢባል ከዓለማችን ቢፈለግ በደረጃ ውስጥ የምትገኘው ኢትዮጵያ ናት።

በአሁን ሰዓት ኢትዮጵያ ሰራተኛው በሰላም ወደ ቤቱ የማይገባባት፣ተማሪው በትምህርት ገበታው የማይገኝባት፣በኑሮ ውድነቱ ረሃብ የነገሰባት የጥቂቶች ባለመብት ሃገር ሆናለች ቢባል ሃሰት አይደለም።

ውድ የሃገራችን ዜጎች

በሃገራችን የ27 ዓመት የትግል ጉዞ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ያለፍርድ ተገለዋል፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ተሰደዋል፣በርካቶች ታስረዋል፣በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ስራ አጥ ሆነዋል፣ህዝባችንን በመከፋፈልና ቡደንተኛ ለማድረግ በገዢው የህውሃት መንግስት ሌት ተቀን በዜና ማስረጫው የሚነዛው መርዝ ወቅቱን ጠብቆ እየፈነዳ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

በአሁን ሰዓት የወያኔ ኢሃዴግ አንባገነን መንግስት ``በአባይ ግድብ ምክናየት ግብጽ ልትወጋኝ ጦሯን በኤርትራ አስፍራለች፣የኤርትራ መንግስት ጦሯን እያንቀሳቀሰች ነው`` በማለት የሚያሰራጨው መልዕክት ፍጹም ውሸትና ጊዜያዊ የመተንፈሻ ጊዜ ለማግኘት የተጠቀመው ማዘናጊያ መሆኑን ህዝባችን በአንክሮ እንዲገነዘብ በአንክሮ እያሳሰብን

በወያኔ አገልጋይ አጋዚ ወታደሮች የተገደሉ ዜጎቻችንን ሁሌም እያሰብንና ለቤተሰቦቻቸው መጽናናትን እየተመኘን ይህ መግለጫ ከወጣበት ቀን ከታህሳስ 17/2010 እስከ ታህሳስ 25/2010 ለአንድ ሳምንት የሚቆይ የሃዘን ቀን የጠራን መሆኑን እየገለጽን በቀጣዩ ይህን እጅግ መራር ትግል ውጤታማ ለማድረግና ትግሉን አቅጣጫ ለማስያዝ በአንድ ቃል “ኢትዮጵያን እናድን” በሚል መርህ በአንድ ቃል ስረዓቱን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሽቀንጥሮ ለመጣል በያለበት እንዲነሳ  የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ጥሪውን ያስተላልፋል።

አንድነት ሃይል ነው

EPPF

ኢሕአግ

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር